SWEDISH MEDICAL CENTER

ስለ የጤና መረጃ ተግባራት ማስታወቂያ (Amharic)

ይህ መረጃ የእርሶ መረጃ ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችልበትና ይፋ ስለሚወጣበት እንዲሁም ይህን መረጃ እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎን በጥሞና ይመልከቱት።

ስውዲሽ ("ስውዲሽ" ወይም "እኛ") የጤናዎን መረጃዎች በሚስጥር እንዲያስቀምጥ፣ ለሕጋዊ ግዴታዎቹና በሚስጥር የማስቀመጫ ተግባራትን፣ እና በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለጹትን የመረጃ ተግባራትን እንዲከተል በሕግ ይጠበቅበታል። ይህ ማስታወቂያ የጤና መረጃዎ እንዴት ለጥቅም ሊውል እንደሚችል እና/ወይም ይፋ ሊወጣ እንደሚችል፣ እና ለዚህ ማስታወቂያ ቅጅ ለመጠየቅና ለመቀበል መብት እንዳለዎት ያብራራል። በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ እንደተገለጸው በስተቀር ስውዲሽ የጤና መረጃዎን አይጠቀምበትም ወይም ይፋ አያወጣም።

ይህ ማስታወቂያ በጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች፣ በሠራተኞች፣ በተኮናታሪ ሠራተኞች፣ በተማሪዎች እና በፈቃደኛ ሠራተኞች ለስውዲሽ በሆነ አካል በመነጨት ሁሉም መረጃዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣ የሚከተሉትንም ጨምሮ፥

- ስውዲሽ ሜዲካል ሲንተር ሆስፒታል ካምፓስ
- ስውዲሽ አምቦላቶሪ ኬር ሴንተርስ
- ስውዲሽ ሜዲካል ግሩፕ
- ስውዲሽ ቪዚቲንግ ነርስ ሰርቪስስ
- ስውዲሽ ኢንስትቲዩትስ
- ስውዲሽ ክልኒክስ

ይህ ማስታወቂያ አንድን የታካሚ የኤሌክትሮኒክ የጤና መረጃ ከስውዲሽ ጋር ለመካፈል ስምምነት ላደረጉና የዚህን ማስታወቂያ የጤና መረጃ ተግባራትን በሚያከብሩ በሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የስውዲሽ አካል ለሆኑና የስውዲሽን የታካሚ የኤሌክትሮኒክ የጤና መረጃ ሥርዓትን የሚካፈሉ ለሌሎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች የተሟላው ዝርዝር በስውዲሽ ዌብሳይት ላይ ይገኛል፥ www.Swedish.org

ይህ ማስታወቂያ በእነዚህ አገልግሎት መስጪያዎችና ከእነሱ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ክልኒኮችና ጽ/ቤቶች ውስጥ ለእርሶ እንክብካቤ ጥቅም ላይ ለዋሉት የግል ጤና መዝገብ መረጃና የጤና መዝገቦች ተፈጻሚ ይሆናል። በተለይም፣ ይህ የመዝገብ መረጃ የእርሶን የሕመም ምልክቶች፣ የምርመራና የምርመራ ሙከራ ውጤቶችን፣ የሕመም ምልክት ምርመራ ውጤቶችን (ዳይግኖሲስ)፣ ሕክምናን፣ እና የወደፊት እንክብካቤ ወይም ሕክምና ዕቅድን ይይዛል። በሆስፒታሉ፣ በድንገተኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መዝገቦች፣ እና እንደ ኤክስ-ሬይ እና የተመላላሽ ታካሚ ክልኒኮች የመሰሉት የሕመም መመርመሪያ ክፍሎች ምሳሌዎች ናቸው። በእነዚህ አካሎች መካከል የጋራ የጤና እንክብካቤ ዝግጅት ስናቀርብ፣ የሕክምና፣ የክፍያ እና የሥራ ተግባራትን ለመፈጸም እንዳስፈላጊነቱ የጤና መረጃዎን እናካፍላለን።

ይህ ማስታወቂያ ለስውዲሽ የኤሌክትሮኒክ የጤና መዝገብ መረጃ ሥርዓት ተፈጻሚ ይሆናል። እያንዳንዱን የታካሚ የኤሌክትሮኒክ የጤና መዝገብን ለሕክምና ጉዳዮች ማግኘት ይቻላል። አንዳንዶቹ ምሳሌዎች፥

- ማይቻርት (MyChart) ተብሎ በሚጠራ በተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት በታካሚ ወይም የታካሚ ፈቃድ ባለው ተወካይ፣ ወይም
- በተጠበቀ ከሩቅ መረጃን በማግኛ ዘዴ ወይም በሌላ የተጠበቀ መረጃ ማውጫ ወይም መለዋወጫ ሂደት ባንድ አገልግሎት አቅራቢ ወይም ከታካሚው የሕክምና ግንኙነት ባለው በሌላ የጤና እንክብካቤ ባለሙያ።

የግል የጤና መረጃን መጠቀም

አንድን ሆስፒታል፣ ሐኪም፣ ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢን በሚጎበኙበት በእያንዳንዱ ጊዜ ላይ ለጉብኝትዎ ምዝገባ ይደረጋል። ይህ መረጃ ብዙውን ጊዜ የጤናዎ ወይም የሕክምና መዝገብ መረጃዎ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለሚከተለው ያገለግላል፥

- ለእንክብካቤዎ እና ለሕክምናዎ ዕቅድ ማውጫ
- ለጤና እንክብካቤዎ ለሚያበረክቱት ለብዙዎች የጤና ባለሙያዎች ግንኙነት ማድረጊያ በመሆን

- ያገኙትን እክብካቤ የሚገልጽ ሕጋዊ ሰነድ በመሆን
- እርሶ ወይም ሦስተኛ-ወገን ሂሳብ ከፋይ ወጪው የተጠየቀባቸው አገልግሎቶች በእርግጥ ቀርበው ለመሆናቸው ማረጋገጫ በመሆን
- የጤና ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለማስተማሪያ መርጃ መሣሪያ
- ለሕክምና ምርምር የአሃዛዊ መረጃ ምንጭ በመሆን
- ለሃገር ውስጥ የጤና መሻሻል ኃላፊነት ለተሰጣቸው የሕዝብ የጤና ሹሞች የመረጃ ምንጭ በመሆን
- ለአገልግሎት መስጪያና ለገበያ ማስታዋወቂያ የአሃዛዊ መረጃ ምንጭ በመሆን
- የምናቀርብውን እንክብካቤና የምናገኛቸውን ውጤቶች ለማሻሻል ማግኘት የምንችልበትና ያለማቋረጥ ሥራ የምንሠራበት መርጃ በመሆን

በመዝገብ መረጃዎ ውስጥ ምን እንዳለና የጤና መረጃዎ እንዴት ለጥቅም እንደሚውል ማወቁ ለሚከተለው ይረዳዎታል፥

- ትክክለኛነቱን እርግጠኛ እንዲያደርጉ
- የጤና መረጃዎን ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ ለምን፣ እና እንዴት ሌሎች ማግኘት እንደሚችሉ በተሻለ መንገድ እንዲረዱ
- ሌሎች መረጃዎን ይፋ እንዲወጣ ፈቃድ ሲሰጡ በማወቅ ተጨማሪ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ

ሕክምና፣ ሂሳብ ክፍያ እና የጤና ድርጊቶችን ይፋ የማውጣት ምሳሌዎች

የሚከተሉት ምድቦች የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበትና ይፋ ልናወጣበት የምንችልባቸውን መንገዶች ይገልጻሉ።

ሕክምና። ለእርሶ የጤና አገልግሎቶችን ለማቅረብ የጤና መረጃዎን እንጠቀማለን። ለምሳሌ፣ ነርሶች፣ ሐኪሞች ወይም ሌሎች የጤና እንክብካቤዎ ቡድን አባላት በመዝገብ መረጃዎ ላይ የጤና መረጃዎን ይመዘግቡና ያንኑ መረጃ ለሚከተለው ይጠቀሙበታል፥ ለሕክምና፣ ለምርመራ፣ ለቴራፒዎችና የመድሐኒቶችን ዓይነት ለማወቅ፤ ሕክምናን ለማካሄድ፤ እና በሕክምናው የሚያሳዩትን ለውጥ ሁኔታ ለመረዳትና ለመገምገም። ደግሞም ከስውዲሽ ለቀው ከወጡ በኋላ በእርሶ የሕክምና እንክባካቤ ተካፋይ ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች የጤና መረጃዎን ልንገልጽ እንችላለን፣ ለቤተሰብ አባላትና ለሌሎች የጤና እንክባካቤ አቅራቢዎች ለመስሉት።

ሂሳብ ክፍያ። የጤና መረጃዎን ለሂሳብ ክፍያ እንጠቀምበታለን። ለምሳሌ፣ ሂሳብ ማስከፈያ (ቢል) ለእርሶ ወይም ለሦስተኛ-ወገን ከፋይ ሊላክ ይችላል። በሂሳብ ማስከፈያው ወይም በአባሪው ላይ ሂሳብ ማስከፈያው (ቢሉ)፣ እርሶን፣ የሕመምዎን ምርመራ ውጤት፣ የአገልግሎቶች ቀኖች፣ የተደረጉ ሕክምናዎች (ፕሮሲጀር) እና ለአገልግሎት የዋሉ ቁሳቁሶችን የሚገልጽ መረጃ ሊጨምር ይችላል።

የተለመዱ የጤና እንክብካቤ ድርጊቶች። የጤና እንክብካቤ ድርጊቶችን ለማካሄድ የጤና መረጃዎን እንጠቀማለን። ለምሳሌ፣ የሕክምናው ሠራተኞች አባላት፣ ወይም የጥራት ማሻሻያ ቡድን፣ በጤና መዝገብ መረጃዎ ውስጥ ያለውን መረጃ በእርሶ ጉዳይና በሌሎች በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ያለውን እንክብካቤና ውጤቶቹን ለማግኘት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህ ሠራተኞቻችን ለእርሶ እንክባካቤ ሲያቀርቡ ያደረጉትን ተግባር ለመገምገም ይረዳል።

ሌሎች መጠቀሚያዎችና ይፋ ማውጫዎች

ደግሞም ያለ እርሶ ስምምነት ልዩ ዓይነት ዘገባ የማቅረቢያ ነጥቦችን ለማሟላት፣ እንክብካቤው መቀጠሉን ለማስቻል፣ ወይም ለሕዝብ የጤና ወይም ሌሎች ጉዳዮች የግል ጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም ልንገልጽ እንችላለን። እንደዚህ ዓይነቶቹ መጠቀሚያዎች ወይም ይፋ ማውጫዎች የሚጨምሩት፥

- በጤና እንክባካቤዎ ላይ ተካፋይ የሆኑ ቤተሰብ፣ የኑሮ አጋርዎ እና ጓደኞች
- የድርጅታችን የሥራ አባላት፣ ለአገልግሎቶቻችን ኮንትራት የምንሰጣችው። የድርጅት አባላት ምሳሌዎች፣ አማካሪዎች፣ ሂሳብ ሠራተኞችን (አካውንታንት)፣ ጠበቃዎች፣ የሕክምና መረጃ ጻሐፊዎችና ሦስተኛ ወገን የሂሳብ ክፍያ (ቢል) ኩባንያዎች ናቸው። እነዚህ የሥራ አባላት የጤና መረጃዎን ሚስጥር እንዲጠብቁ እንጠይቃቸዋለን።
- የፋድ ኤንድ ድራግ አድምንስትሬሽን፣ ክፉኛ ሁኔታዎችን ለማሳወቅ
- ለጤና ቁጥጥር ተግባራት አሃዛዊ መረጃ፣ ለኦዲት ወይም ለንግድ ፈቃድ (ላይሰንስ)

- ለተላላፊ በሽታዎች ዘገባዎች
- ከሥራ ጋር ለሚገናኙ ሕመሞች ወይም ጉዳቶች ለአሠሪ መሥሪያ ቤቶች ዘገባዎች
- ስለ ማጎሳቆል፣ ያለጠባቂ የመተው ወይም የቤት ውስጥ ተጠቂ ዘገባዎች
- በጤና ወይም በደህንነት ላይ ከፉኛ አደጋን ለማከሸፍ ወይም በአንድ ግለሰብ ላይ ሊመጣ የሚችልን ከፉኛ ጉዳት ለመከላከል
- የአደጋ (መዓት) ማስታገሻ፣ ያሉበትን ቦታና አጠቃላይ ሁኔታዎችን ለሕዝብ ወይም በአደጋ ማስታገሻ ጥረት ላይ እንዲረዳ በሕግ ለተፈቀደለት ለግል አካል (እንደ ፊማ ወይም ቀይ መስቀል ለመሰሉት) ልናሳውቅ እንችላለን
- በሕግ እንደሚጠየቀው፣ ለሕግ ማስከበሪያ ለመሰሉት ወይም ለፍርድ ቤት መጥሪያ ወይም የፍርድ ቤት ትዛዝን ለማክበር
- በሆስፒታል ዝርዝር መግለጫ መረጃ፣ በስምዎና ባጠቃላይ የሕመም ሁኔታዎ የተወሰነ (ማለትም፣ “ጽኑ፣” “ደከም ያለ፣” “ደህና፣” “ጥሩ፣” ወይም የመሳሰሉትን ዓይነት መግለጫዎች)፣ ከዝርዝር መግለጫው ስምዎ እንዲወጣ እንደሚፈልጉ ካላሳወቁን
- ስለ የሞተ ሰው (ሙት) መሪማሪዎች ወይም የሕክምና መርማሪዎች፣ የሥራ ግዴታቸውን እንዲያከናውኑ፣ እንዳስፈላጊነቱ
- የሰውነት ውስጥ አካልን(ኦርጋን) ለሚወስዱ ድርጅቶች፣ በሕግ እስከሚፈቀደው ድረስ
- በተቋም አጥኝ ቦርድ እንደተፈቀደው ለምርምር። አብዛኞቹ የክልኒክ የምርምር ጥናቶች በግልጽ የታካሚ ስምምነት እንዲኖር የሚጠይቁ ቢሆንም፣ አንድ የመዝገብ መረጃ፣ የሰውነት ሥጋ (ቲሹ)፣ ስፔሲሜን (የሰውነት ቅንጣት ናሙና) ያለ ታካሚው ስምምነት የሚጠኑባቸው ሁኔታዎች አሉ
- ለልዩ ዓይነት የመንግሥት ጉዳዮች፣ ለምሳሌ፣ በውትድርና ባለሥልጣኖች እንደሚጠየቀው
- ለሠራተኛ መደጎሚያ
- ገንዘብ ለማዋጣት፥ ገንዘብ ለማዋጣት ለሚደረገው ጥረት ልናነጋግርዎት እንችል ይሆናል
- ለገበያ ማስተዋወቂያ፥ ስለ ሕክምና አማራጮች ወይም ሌሎች ሊፈልጓቸው ለሚችሉት ከጤና ጋር ለሚገናኙ አገልግሎቶች መረጃ ልናቀርብልዎት እንችላለን
- ቀጠሮ ማስታወሻዎች
- እስረኛ ከሆኑ የጤና መረጃዎ ለፀባይ ማረሚያ ተቋም ወይም ወኪል መሥሪያ ቤቶች ሊሰጥ ይችል ይሆናል

ሌሎች መጠቀሚያዎችና ይፋ ማውጫዎች በእርሶ የጽሑፍ ፈቃድ ብቻ የሚደረጉ ይሆናሉ፣ ባብዛኞቹ ሁኔታዎች ላይ ፈቃዱን የመሻር መብት አለዎት።

ልዩ ፈቃድ መስጫያዎች

ለተወሰኑ ዓይነት የግል የጤና መረጃዎች ልዩ ዓይነት ጥበቃ የሚያደርጉ የፌደራል እና የስቴት ሕጎች (እንደ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች፣ የጎጂ ዕጽ (ድራግ) እና አልኮሆል አላግባብ መጠቀም ሕክምና፣ ለተወሰኑ የአእምሮ ጤና ሕክምና አገልግሎቶች ለመሰሉት) መረጃው እንዲገለጽ ከእርሶ በግልጽ ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ። የግል ጤና መረጃዎ በነዚህ ልዩ የሆነ መጠበቂያዎች ሥር በሚሆን ጊዜ፣ ሕጎቹን ለማክበር አስፈላጊዎቹን ፈቃዶች ከእርሶ እንድናገኝ እናደርጋለን።

መብቶችዎ

የግል የጤና መረጃዎ ጥቅም ላይ ስለሚውልበትና ይፋ ሰልሚወጣበት ሁኔታ የግል መብቶች አሉዎት፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መብቶችንም ጨምሮ። ለእኛ የሔልዝ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ዲፓርትመንት በ (425) 640-4200 በመደወል ከእነዚህ መብቶች ውስጥ አንዳቸውንም ቢሆን ለማስከበር ይችሉ ይሆናል።

ውስን መጠቀሚያ፥ በጽሑፍ በመጠየቅ መረጃዎን ለሕክምና፣ ለሂሳብ ክፍያና ለአስተዳደር ጉዳዮች እንዳንጠቀምበት ወይም ይፋ እንዳናወጣ ሊያድረጉ ይችሉ ይሆናል፣ በእርሶ በግልጽ በሚፈቀድ ጊዜ፣ በሕግ በሚያስፈልግ ጊዜ፣ ወይም በድንገተኛ ሁኔታዎች ጊዜ በስተቀር። ጥያቄዎን እናስብበታለን ግን እንድንቀበለው በሕግ አንገደድም።

የግል-ክፍያ መወሰኛ፥ በግል ወጪ ሂሳቡ ለተከፈለላቸው አገልግሎቶችና ቁሳቁሶች የግል የጤና መረጃዎን ለጤና ፕላኖች (ኢንሹራንስ) እንዳናሳውቅ በጽሑፍ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችሉ ይሆናል። ጥያቄዎን ለማክበር እንድንችል መሟላት የሚያስፈልጋቸው የተውሰኑ ሁኔታዎች አሉ።

የሚስጥር መልክቶችን መቀበል፥ አማራጭ በሆነ መንገድ ወይም ቦታዎች በሚስጥር መልክቶችን የመቀበል መብት አለዎት። ይህ አማራጭ የሆነ የፖስታ አድራሻ ወይም ኢሜይል አድራሻን ሊጨምር ይችላል።

ምርመራ እና ቅጅ (ኮፒ)፥ ላብዛኞቹ ጉዳዮች፣ የጤና መረጃዎን ለማግኘት ወይም ኮፒውን ለማግኘት በጽሑፍ የመጠየቅ መብት አለዎት።

ማረሚያዎችን መጠየቅ፥ በመዝገብ መረጃዎ ላይ ተሳስቷል ብለው የሚያምኑበትን መረጃ እንድናስተካክል ወይም ጠፍቷል ብለው የሚያምኑበትን መረጃ እንድንጨምር በጽሑፍ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዎት።

ይፋ ስለወጡ መረጃዎች ማወቅ፥ ለሕክምና፣ ለሂሳብ ክፍያ ወይም ግንኙነት ላላቸው የአስተዳደር ጉዳዮች በስተቀር ለሌሎች ምክንያቶች መረጃን ይፋ ላወጣንባቸው ሁኔታዎች ዝርዝር በጽሑፍ ጥያቄ የማቅረብና የማግኘት መብት አለዎት።

አቤቱታዎች፥ የግል ሚስጥርዎን እንደጣስን የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ ወይም የመዝገብ መረጃዎን ስለማግኘት ባደረግነው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ለታካሚ ግንኙነት ጽ/ቤታችን በ (206) 386-2111 መደወል ወይም ለግል ሚስጥር ጉዳይ ጽ/ቤታችን (ፕራይቬሲ ኦፊስ) በ (206) 386-6178 መደወል ይችላሉ።

የሴክሬታሪ ኦፍ ሔልዝ ኤንድ ሂውማን ሰርቪስስን ሊያነጋግሩም ይችላሉ - የኦፊስ ኦፍ ሲቭል ራይትስ፣ የግል ሚስጥር መብቶችዎ እንደተጣሱ ከተሰማዎት። ማንኛውንም አቤቱታ በማቅረብዎ ስውዲሽ በእርሶ ላይ አጸፋውን አይመልስም።

የመረጃዎን ሚስጥረኛነት እንድንጠብቅ፣ ስለ ጤና መረጃ ተግባሮቻችን ይህን ማስታወቂያ እንድናቀርብና በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለጹትን የግል ሚስጥር ተግባራትን እንድንከተል በሕግ እንጠየቃለን።

ለዚህ ማስታወቂያ ለውጦች

ይህ ማስታወቂያ ከሚያዚያ 14, 2003 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል። የዚህን ማስታወቂያ ቃሎች ለመቀየርና በምናስቀምጣቸው ሁሉም የግል የጤና መረጃዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ አዲስ የማስታወቂያ አንቀጾችን ለማድረግ መብታችን የጠበቀ ነው። የተከለሰው ማስታወቂያ በአገልግሎት መስጪያ ቦታዎቻችንና በዌብሳይታችን www.swedish.org ላይ ይወጣል። ለወቅታዊው የማስታወቂያ ቅጅ በ (206) 386-2502 በማንኛውም ጊዜ ላይ ደውለው ሊጠይቁ ይችላሉ።
Rev. 03-25-2011